# የልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት
# የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች
# አፈፃፀም መመሪያ

## ( የመጨረሻ ረቂቅ)

ትምህርት ሚኒስቴር

በልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

የካቲት 2004

አዲስ አበባ

## ማውጫ


አርዕስት ገጽ

1. መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------------ 1
   - 1.1 ልዩ ትምህርት------------------------------------------------------------ 2
   - 1.2 ልዩ ፍላጎት ትምህርት ------------------------------------------------- 2
   - 1.3 አካቶ ትምህርት ------------------------------------------------------- 2
2. የመመሪያው አስፈላጊነት ---------------------------------------------------------------- 3
3. የመመሪያው ዓላማ ------------------------------------------------------------------------ 4
4. የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሁኔታ በኢትዮጵያ ------------------------------ 5
5. የኮሚኒዩኬሽን ምንነትና የአፈፃፀም ሥልቶች ------------------------------------ 9
   - 5.1 የኮሚኒዩኬሽን ምንነት ------------------------------------------------------------ 9
   - 5.2 የኮሚኒዩኬሽን መርሆዎች ------------------------------------------------------ 10
   - 5.3 የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽንና የግንዛቤ ማስጨበጫ አፈፃፀም ስልቶች ---------------------------------- 11

6 በኮሚኒዩኬሽንና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ------------------------------------------------ 15
   - 6.1 ትምህርት ሚኒስቴር ---------------------------------------------------------- 15
   - 6.2 ክልል ት/ቢሮዎች -------------------------------------------------------------- 16
   - 6.3 ወረዳ ት/ጽ/ቤቶች -------------------------------------------------------------- 17
   - 6.4 ትምህርት ቤቶች --------------------------------------------------------------- 19
   - 6.5 መደበኛና የልዩ ትምህርት መምህራን ----------------------------------------- 19
   - 6.6 ወላጆች ------------------------------------------------------------------------------ 20
   - 6.7 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት ------------------------------------------------ 20
   - 6.8 ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ------------- 21

7 ክትትልና ግምገማ ------------------------------------------------------------------ 22

## 1.መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ዜጎች መንግሥት ባዘጋጃቸው የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ሁሉ ዕኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸውና በተለይም ለአካል ጉዳተኞች አቅም በፈቀደ መሰረት ድጋፍ እንደሚያደርግ ይደነግጋል (አንቀፅ 41 ንዑስ አንቀፅ 5)፡፡ በ1986 ዓ.ም በወጣው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲም አካል ጉዳተኛና ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው ህፃናት እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው እንደሚማሩ ተደንግጓል፡፡ ይህ ህገ መንግስታዊ መብትና የፖሊሲ አቅጣጫ በግልፅ ቢቀመጥም ትምህርትን ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ለማዳረስ ገና ረጅም መንገድ መጓዝ እንዳለብን ያስገነዝባል፡፡

በአገራችን አካል ጉዳተኝነት በውል ያልታወቀና በህብረተሰቡም ዘንድ ትኩረት ያልተደረገበት በመሆኑ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የአካል ጉዳተኞችን የትምህርት ሁኔታ የሚገልፅ የተቀናጀ የትምህርት መረጃ ባይኖርም ትምህርት ሚኒስቴር ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በአካል ጉዳተኛ ህጻናት የትምህርት ተደራሽነት ዙሪያ መረጃ ማሰብሰብ ጀምሯል፡፡ በ2002 ዓ.ም ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መረጃ መሰረት የአካል ጉዳተኛ ህጻናት የትምህርት ተደራሽነት 2.8 በመቶ ገደማ ነው፡፡፡

የትምህርት ለሁሉም ግብን ለመምታትና ያለውን ክፍተት ለማጥበብ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂ ቢዘጋጅም የአካል ጉዳተኛ ህጻናትና ወጣቶች የትምህርት ተሳትፎ የተጠበቀውን ያህል ሊሆን አልቻለም፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የህብረተሰቡ በአካል ጉዳት አመጣጥና በአካል ጉዳተኛ ህፃናትና ወጣቶች ትምህርት የተሳሳተ ግንዛቤ መያዝ፣ በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላት፣ መምህራን፣ ሌሎች ባለድርሻዎች የጠራ ግንዛቤ አለመያዝ፣ የግባዓት አቅርቦት ችግር፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣ የትምህርት ቤቶች ተደራሽ አለመሆን፣ የት/ቤቶች አመራሮችና መምህራን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጁ አለመሆን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡፡ (ወቅታዊ ሁኔታ ትንተና 2000 ዓ.ም)

ይህንን አሉታዊ አመለካከት ለመቅረፍና የአካል ጉዳተኛ ህፃናትን የትምህርት ተሳትፎ ለማሳደግ ለማህበረሰቡ፣ በየደረጃው ላሉ የአመራር አካላት፣ ለመምህራንና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የታቀደ፤ የተቀናጀ፣ የተጠናከረና የተደረጀ የአህዝቦት ስራ ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊከናወን የሚገባ ጉዳይ ሆኗል፡፡ ስለሆነም፤ የኮሚዩኒኬሽንና የአህዝቦት ስራ ለመፈፀም ያስችል ዘንድ ይህን የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚዩኒኬሽን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡

### 1.1 ልዩ ትምህርት

ልዩ ትምህርት ስንል የመማር ችግር ያለባቸውንና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ልዩ ፍላጎት በሚያረካ መልኩ በልዩ ትምህርት ቤቶች፤በልዩ ዩኒቶችና በልዩ ክፍሎች ትምህርት የሚሰጥበት የትምህርት አደረጃጀት ነው፡፡ በእነዚህ ልዩ ትምህርት ቤቶችና ክፍሎች የሚያስተምሩ መምህራን በአብዛኛው የተለየ

ስልጠና የወሰዱ ከመሆናቸው ባሻገር ተማሪዎቹም የተለያዩ ባለሙያዎችንና ወጌሻዎችን የመጎብኘት ዕድል አላቸው፡፡ በዚህ የትም/ አሰጣጥ ሂደትም የተማሪ መምህር ጥምርታው ከመደበኛው በጣም ያነሰ ነው፡፡ሆኖም ግን ይህ የትምህርት አደረጃጀት ተማሪዎቹ ለብቻቸው ተገልለውና እራሳቸውን ከት/ቤቱ ፍላጎት ጋር አስማምተው የሚማሩበት አካሄድ በመሆኑ አሉታዊ ገፅታን የተላበሰ ነው፡፡

## 1.2 ልዩ ፍላጎት ትምህርት

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ልዩ ትምህርት ተማሪዎቹ እራሳቸውን ከት/ቤቱ ፍላጎት ጋር አስማምተው የሚማሩበት አደረጃጀት ስለሆነ በተማሪዎቹ ላይ የሚታዩት የመማር ችግሮች ምንጫቸው የት/ቤቶች አደረጃጀት፣ የማስተማሪያ ዘዴው ተለማጭ አለመሆንና የስርዓተ ትምህርቱ ግትርነት ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ጥናቶች ያመላከቱ ሲሆን ብዝሃ ፍላጎትንና በተማሪዎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ለማስተናገድ ትምህርት ቤቶች አደረጃጀታቸውን የመለወጥ፣ የትምህርት አቀራረቡንና የማስተማሪያ ዘዴውን እንዲሁም ስርዓተ ትምህርቱን የማሻሻልና ትምህርቱን በተሟላ መልኩ ለመስጠት ያስችል ዘንድ በልዩ ፍላጎት ትምህርት መርህ መመራትን አስከትሏል ፡፡ ስለዚህም፤ ባሁኑ ጊዜ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አደረጃጀት ከልዩ ትምህርት አደረጃጀት የተለየ በመሆኑ የተለያዩ የትምህርት እርከኖችን በማስተናገድ ላይ ይገኛል፤ ይህም ከልዩ ትምህርት ቤቶችና ልዩ ክፍሎች ጀምሮ፤ እስከ አካቶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የመማር ችግሮች ያሉባቸውንና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ያጠቃልላል፡፡

## 1.3 አካቶ ትምህርት

አካቶ ትምህርት ማለት ሁሉም ተማሪዎች /አካል ጉዳተኞችም ሆኑ ጉዳት አልባ ተማሪዎች/ በአቅራቢያቸው በሚገኙ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተካተው ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚማሩበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡"ይሁን እንጂ የተለያዩ ፀሐፍት አካቶ ትምህርትን ከተለያዩ አውዶች ወይም የትኩረት ነጥቦች /ከትምህርት ተደራሽነት ፣ ከትምህርት አደረጃጀት፣ ከድጋፍ አሰጣጥ ፣ ወዘተ / አንፃር ትርጉም ስለሚሰጡት አካቶ ትምህርት ትርጉሙ ውስብስብ ሊሆን ችሏል፡፡ ስለሆነም ለዚህ መመሪያ ዝግጅት ከዚህ በታች የቀረበውን የዩኔስኮ የ2005 (እአአ) ትርጉም ተጠቅመናል፡፡

> *"ማካተት ማለት የትምህርት ቅስሞሽን፣ የባህልና የማህበረሰብ ተሳትፎን በማሳደግ፣ እንዲሁም ከትምህርት መገለልን በመቀነስ የሁሉንም ተማሪዎች ብዝሃ ፍላጎት ለማስተናገድ የሚያስችል* ***ሂደት*** *ከመሆኑም ባሻገር የመደበኛ ትምህርት ሥርዓት አካል ነው፡፡"*

ይህም መደበኛው የትምህርት ሥርዓት አግባብነት ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናትን በሙሉ የማስተማር የጋራ ራዕዩና ኃላፊነቱን ከመወጣት አኳያ በትምህርት ይዘቶች፣ በትምህርት አቅርቦት

መንገዶች፣በትምህርት አወቃቀሮችና ስትራቴጂዎች ላይ አስፈላጊ ማሻሻያዎችና ለውጦች ማድረግን ያካትታል፡፡

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

በሀገራችን የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት አተገባበር ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ሆነው ከኖሩት ዋነኞቹ ችግሮች መካከል የአመለካከት፣ የግንዛቤና የክህሎት ክፍተቶች ናቸው። የአካል ጉዳተኞችንና ከትምህርት የተገለሉ ህፃናትን የትምህርት አገልግሎት ተጠቀሚ ለማድረግ እነዚህን ክፍተቶች መሙላት ያስፈልጋል። ይህንንም ሁኔታ እውን ለማድረግ ደግሞ የተለያዩ የመግባቢያ ስልቶችን በመጠቀም **በሁለትዮሽ** ተግባቦት ላይ የተመሠረተ የጋራ መግባባትና መተማመንን በመፍጠር፣ እንዲሁም የዕውቀትና የክህሎት ሽግግርን በማስፋት ቀጣይነትና ትርጉም ያለው አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት መሥራት የማይታለፍ ተግባር ይሆናል። ከዚህ አንፃር ኮሚኒዩኬሽን መተኪያ የሌለው መሣሪያ ነው። ዘርዘር ባለ አገላለጽ ኮሚኒዩኬሽን፤

- ህብረተሰቡ በአካል ጉዳት አመጣጥና በአካል ጉዳተኛ ህፃናት ላይ ያለውን አሉታዊ አመለካከት ለማስተካከል፣ የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ተምረው መለወጥ የሚችሉና በሀገራቸው የልማት እንቅስቀሴ ውስጥ ከሌሎች ጉዳት አልባ እኩዮቻቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉና ለዚህም እኩል መብት ያላቸው ስለመሆኑ ግንዛቤ ለማስያዝ፣
- በየደረጃው ባሉ የአመራር አካላት ዘንድ የሚታየውን የእውቀት፣የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት በመሙላት በትምህርት ፖሊሲው፣ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑና የጋራ መግባባትና መተማመንን በመፍጠር / በማጠናከር ሥራውን በቁርጠኝነት በባለቤትነት ስሜት እንዲመሩት ለማስቻል፣
- በየደረጃው የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሥራ በዕቅድና በበጀት ተደግፎ መከናወን እንዳለበት በአመራሩ መካከል መግባባት ለመፍጠር፣
- የትምህርት ቤቶች አመራር አካላትና መምህራን ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ተገቢ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩና የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተናገድ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማስቻል፣
- በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ቅንጅትና ትብብር ለማጠናከር፣
- ተዋረዳዊና የጎንዮሽ የዕውቀትና የክህሎት ሽግርርን በማስፋትና ቀጣይነትና ትርጉም ያለው አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት፣

- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ስትራቴጂና መመሪያዎችን መተግበር የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትና ወደ ሥራ የሚሰማራበትን ሁኔታ ለማመቻቸት አስፈላጊ ይሆናል።

3. የመመሪያው ዓላማ

- በየደረጃው ያሉ የአመራር አካላትን፣ የመምህራንና የህብረተሰቡን አመለካከትና ግንዛቤ በማጎልበት ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና የትምህርት እድል ያላገኙ ህፃናትና ወጣቶች የትምህርት ተደራሽነት ማሳደግና ተገቢና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ማስቻል፣
- በባለድርሻዎች መካከል በልዩ ፍላጎት/አካቶ ትምህርት ላይ በመግባባትና በመተማመን ላይ የተመሰረተ ቅንጅታዊ የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣

4. የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሁኔታ በኢትዮጵያ

የልዩ ፍላጎት ትምህርት በኢትዮጵያ ከተጀመረ አንድ ምዕት ዓመት ገደማ ቢጠጋውም የአካል ጉዳተኛና የተለየ የትምህርት አቀባበል ያላቸው ሕፃናትና ወጣቶች የትምህርት ዕድል ጉዳይ በፖሊሲና ስትራቴጂ ተደግፎ ባለመሰጠቱ አካል ጉዳተኞች የመማር ዕድል አግኝተው አቅማቸውን በማጎልበት በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የመሆናቸው ዕድል እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡ ልዩ ፍላጎት ያላቸውንና የትምህርት እድል ያላገኙ ሕፃናትን በትምህርት የማሳተፍ ጉዳይ በአገሪቱ የትምህርት ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውስጥ ተካቶ የወጣው በ1986 ዓ.ም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ውስጥም፤

- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናትና ወጣቶች ልዩ ትምህርትና ሥልጠና የሚሰጣቸው መሆኑን፣ (ቁጥር 3.2.9)
- አካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው ህፃናት እንደ ፍላጎታቸውና ችሎታቸው መማር እንዲችሉ የሚደረግ መሆኑን፣ (ቁጥር 2.2.3)
- በመደበኛ የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ውስጥ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን የሚሰለጥኑ መሆኑን፣ (ቁጥር 3.4.11)
- ለልዩ ፍላጎት ትምህርት የድጋፍ ግብዓቶች ዝግጅትና አጠቃቀም ልዩ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ (ቁጥር 3.7.6)

ይህንንም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በ1998 ዓ.ም የልዩ ፍላጎት ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ ተቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የስትራቴጂው ግብም የትምህርት እድል ባላገኙ

፣ በአካል ጉዳተኞችና በጉዳት አልባ ህፃናት መካከል ያለውን የትምህርት ተደራሽነት ክፍተት በማጥበብ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥና ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት ነው፡፡ ይህን ዓላማ እውን ከማድረግ አንፃር፡

- በሁሉም የመምህራን ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ዕጩ መምህራን የልዩ ፍላጎት ትምህርት የማስተዋወቂያ ኮርስ መሰጠት መጀመሩ፣
- በአምስት ዩኒቨርሲቲዎችና በስድስት የመምህራን ትምህርት ተቋማት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ክፍል በመክፈት ከዲፕሎማ እስከ ፒ.ኤች.ዲ የትምህርት ደረጃ ድረስ ሥልጠና መሰጠት መጀመሩ፣
- በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሥነ ልሳን ዲፓርትመንት የምልክት ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ መሰጠት መጀመሩ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት መስማት ለተሳናቸው የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የትርጉም አገልግሎት የሚሰጥ የፕላዝማ ሥርጭት ፕሮግራም መጀመሩ፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ የክልሎችን  የማስፈፀምና የመፈፀም አቅም ለመገንባት ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች መሰጠታቸው ከተደረጉ ጥረቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በዘርፉ የሚጠበቀውን ያህል ውጤት ለማስመዝገብ ገና ብዙ መስራት እንዳለብን የሚያስገነዝቡን ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል በ2003 የትምህርት ዘመን  ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ቁጥር  17,341,225 ሲሆን፣ በዓለም ጤና ድርጅት የ10 በመቶ ግምት (WHO 1970 እአአ) መሠረት በዚሁ ዓመት በሀገራችን የሚገኙት የአካል ጉዳተኛ ህፃናት ቁጥር 1,734,122 ነበር፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ የትምህርት ዕድል ያገኙት 55,492  /3.2%/ ብቻ ናቸው፡፡ (ት/ሚ 2004 ዓ.ም የትምህርት ስታቲስቲክስ)፡፡ የአለም ጤና ድርጅት የ2011 (እአአ) ግምት እንደሚያሳየው የአካል ጉዳተኛ ምጣኔ 15% ይደርሳል፡፡ ከዚህ አንፃር ትምህርት ያገኙ የሀገራችን የአካል ጉዳተኞች ምጣኔ ከ3.3% በታች እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በትምህርት አመራር አደረጃጀት፣ የሕብረተሰብ ተሳትፎና የፋይናንስ መመሪያ /ትምህርት ሚኒስቴር 1994 ዓ.ም/ መሠረት ከ1-10ኛ ለሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች በነፍስ ወከፍ 2 የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን እንዲመደቡ ተገልጧል፡፡ በዚህ መሠረት በ2003 የትምህርት ዘመን የነበሩት 29,729 /28,349 የመጀመሪያ ደረጃና 1,380 የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን/ ትምህርት ቤቶች ይገኙ ነበር፡፡ (ት/ሚ 2004 ዓ.ም የትምህርት ስታቲስቲክስ) ለእነዚህ ትምህርት ቤቶች 56,698 በዲፕሎማ የተመረቁና 2,760 በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን የሚያስፈልጉ ቢሆንም፣ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ማሰልጠን የተቻለው ግን ከተቀመጠው ዒላማ አንፃር አመርቂ አይደለም፡፡ ከእነዚህ ምሩቃን መካከል ደግሞ የተወሰኑት በየደረጃው ባሉ አመራር አካላት ግንዛቤ ማነስ ምክንያት ተቀጥረው አገልግሎት ሊሰጡ አልቻሉም፡፡

ከግብዓት አመዳደብ አንፃርም ሲታይ እነዚህን የህብረተሰብ አካላት ከማስተማር አኳያ ለትምህርት የተሰጠው ግምት ዝቅተኛ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በ4ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የተመደበው በጀት ከጠቅላላው የትምህርት ሴክተር በጀት 0.2% መሆኑ ብቻ ሳይሆን ይህንኑ ገንዘብ በትክክል ተግባር ላይ ለማዋል ያለው ተነሳሽነት አናሳ መሆኑ የችግሩን ጥልቀት የሚያመላክት ነው፡፡

በ2000 ዓ.ም በሁሉም የክልል ት/ቢሮዎች፣ ከየክልሎቹ በተመረጡ አንዳንድ የመምህራን ትም/ኮሌጆችና አንዳንድ የቴክኒክና ሙ.ያ ኮሌጆች ላይ በተሰራው የወቅታዊ ሁኔታ ትንተና (situation analysis) ስትራቴጂውን ለመተግበር ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶችን ለመለየት ተሞክሯል። እነዚህንም ተግዳሮቶች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ማለትም በአመለካከት፣ በክህሎትና በግብዓት ከፋፍሎ ማየት ይቻላል።

## 1. <u>የአመለካከትና የግንዛቤ ችግሮች፡-</u>

- የአካል ጉዳት አመጣጥን አለማወቅ ፣
- ማህበረሰቡ ስለልዩ ፍላጎት ያለው ግንዛቤ ውስን መሆን፣ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ዝቅተኛ ግምት መስጠት /ተምሮ መለወጥ አይችሉም ብሎ ማሰብ/
- በየደረጃው ያሉ አመራር አካላትና መምህራን ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ተገቢ ትኩረት አለመስጠትና ስትራቴጂውን ለማስፈፀም ያላቸው ቁርጠኝነት አናሳ መሆን፣
- የሰው ኃይል አሰልጥኖ ለመመደብ የፍላጎት ማነስ፣
- በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ላይ በባለድርሻ አካላት መካከል ቅንጅትና ትብብር አለመኖር፣
- የት/ቤቶች አመራሮችና መምህራን አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጁ አለመሆን፣

## 2 የክህሎት ችግሮች፡-

- በየደረጃው ያሉ የትም/አመራሮችና ባለሙያዎች የልዩ ፍላጎት ትም/ስትራቴጂን ለማስፈፀም ያላቸው አቅም ውስን መሆን፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት፣
- በDisability Specific Skills /ብሬልና የምልክት ቋንቋ/ ላይ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር
- አካል ጉዳተኛ ህፃናትን ለሚንከባከቡ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች /Supportive Staff/ የሥልጠና ሥርዓት ተቀርፆ ማሰልጠን አለመቻል፣
- በተቋማት ደረጃ በሚሰጡ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ኮርሶች ተገቢነትና የአሰለጣጠን ዘዴ ዙሪያ ክፍተቶች በመኖራቸው በተመራቂ ባለሙያዎች ሙያዊ ብቃትና ዝግጁነት ላይ አሉታዊ

ተጽእኖ ማሳደሩ፣(አሠልጣኝ የትምህርት ተቋማት የሥልጠና አሰጣጥ ከአካቶ ትምህርት ይልቅ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ ማተኮሩ፣)

- በየደረጃው የልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርትን በተመለከተ ወጥ የሆነ የክትትልና ድጋፍ ስልት አለመዘርጋት።

## 3 የግብዓት ችግሮች፡-

- ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተደራሽና ምቹ አለመሆን /የትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ የሽንት ቤት አሰራር፣ ቤተ መጽሐፍት፣ ቤተሙከራ፣ ውሃ መጠጫ ቦታ፣ ወዘት አለመሆን/፣
- በክለስተርና በልዩ ትምህርት ቤቶች የድጋፍ መስጫ ማዕከላት አለመቋቋም፣
- በቂ በጀት መድቦ ሥራ ላይ አለማዋል፣
- የትምህርት መሣሪያዎች /የብሬል ወረቀት፣ ስሌት፣ ስታይለስ፣ ወዘተ/ አቅርቦት አለመኖር፣
- ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ድጋፍ የሚሰጡ መሣሪያዎች /ዊልቸር፣ ክራንች፣ ኬን፣ ወዘተ/ አለመኖር፣
- ለአይነ ሥውራን መጠቀሚያነት ተስማምተው/adapted/ ወደ ብሬል የተቀየሩ የመማሪያ መጽሐፍት አለመኖር፣
- መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አለመኖር፣
- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት/አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ/በተመለከተ የመረጃ ክፍተት መኖር ወዘተ ጥቂቶቹ ናቸው፡።

# 5. የኮሚዩኒኬሽን ምንነትና የአፈፃፀም ሥልቶች

## 5.1 የኮሚዩኒኬሽን ምንነት

ኮሚኒዩኬሽንን የተለያዩ አካላት በተለያየዩ መንገዶች ይተረጉሙታል። በአንዳንድ ፀሓፍት አገላለጽ ኮሚኒዩኬሽን ማለት ቋንቋን ወይም ምልክትን በመጠቀም የኢንፎርማሽን፣የሃሳብ ወይም የስሜት ልውውጥን ወይም መልዕክትን ማስተላለፍና መረዳትን ያጠቃልላል፡፡ ይሁን እንጂ የዓለም ባንክ (2008 እኤአ) የሰጠው ትርጉም ከዚህ መመሪያ ጋር ተስማሚ ሆኖ ስላገኘነው እንደሚከተለው ቀርቧል።

> “ኮሚዩኒኬሽን በተጨባጭ ጥናትና የሁለትዮሽ ተግባቦት ላይ በመመስረትና የተለያዩ የመግባቢያ ስልቶችን በመጠቀም በሁለት አካላት መካከል የጋራ መግባባትና መተማመን ለመፍጠር፣ የዕውቀትና የክህሎት ሽግግርን ለማመቻቸት፣ የፖሊሲ ሀሳቦችን ለማመንጨት፣ በልማት

እንቅስቃሴ ውስጥ ቀጣይነትና ትርጉም ያለው አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሳሪያናሂደት ነው ።"

**<u>በትርጉሙ ውስጥ የተጠቀሱ ቁልፍ ቃላት ማብራሪያ</u>**

**"የሁለትዮሽ ተግባቦት"** ማለት የሁለቱን ወገን /ላኪና ተቀባይ/ ተሳትፎ የሚያመላክት የኮሚዩኒኬሽን መንገድ ነው ። ይህም ማለት ኮሚኒዩኬሽን እንዲኖር ከተፈለገ መልዕክቱ ከላኪው ወደ ተቀባዩና ከተቀባዩ ወደ ላኪው አሳታፊ በሆነ መንገድ መተላለፍ ይኖርበታል።

**"የተለያዩ የመግባቢያ ስልቶችን"** ማለት የመግባቢያ ስልቶች መልዕክት የሚተላለፍባቸው ሥልቶች ናቸው ። እነዚህም ንግግርን፣ ጽሁፍን፣ ምልክትን፣ ሥዕልን፣ ወዘተ የሚያካትቱ ሲሆኑ እንደሚተላለፈው መልዕክትና እንደ መልዕክት ተቀባዩ ዓይነት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ስልቶችን መጠቀም ይቻላል።

**"የጋራ መግባባትና መተማመን"** ማለት በመወያየትና በመከራከር ልዩነቶችን አጥብቦ የጋራ ውሳኔ ላይ መድረስ ነው ።

**"የዕውቀትና ክህሎት ሽግግርን ማመቻቸት"** ማለት ዓለም አቀፍና ሀገራዊ መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስተዋወቅ፣ እንዲሁም የተለያዩ የመማማሪያና የእርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማመቻቸት አዳዲስ አስተሳሰቦችንና አሰራሮችን ማስረጽ፣

**"የፖሊሲ ሀሳቦችን ማመንጨት"** ማለት በጥናትና በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱና የወደፊት የልማት አቅጣጫን የሚያመላክቱ የፖሊሲ ሀሳቦችን ማፍለቅ፣

**"ቀጣይነትና ትርጉም ያለው አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት"** ማለት በጋራ መግባባትና መተማመን ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችንና የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ተግባራዊ በማድረግ በልማቱ ዕንቅስቃሴ ውስጥ ዘለቄታ ያላቸው ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ ነው፣

## 5.2 የኮሚዩኒኬሽን መርሆዎች

በኮሚዩኒኬሽን ትርጉም ውስጥ የተካተቱትን ቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ ለማስቻል የሚከተሉትን መርሆዎች በውል ማጤንና ሥራ ላይ ማዋል ተገቢ ይሆናል።

- ታዳሚዎችን /audiences/ ለይቶ ማወቅ
- ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ርዕስና ይዘት ጠንቅቆ ማወቅ
- ለማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ዓላማ ጠንቅቆ ማወቅ

- ተቃውም ሊገጥም እንደሚችል አስቀድሞ መገመት
- የመልዕክቱን ምሉዕ የሆነ ገጽታ ማቅረብ፣
- በታዳሚዎች ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት
- የሀሳብ መዋዠቅን መከላከል/ሀሳብን በግልፅ ማቅረብ/፣
- በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ መልዕክት ማስተላለፍ፣
- መልዕክትን በተለያዩ መንገዶች ማቅረብ፣
- ከታዳሚዎች ግብረ-መልስ/ቀጥተኛና የዘገየ/ ለማግኘት የሚያስችሉ ተግባራዊና ጠቃሚ ዘዴዎችን መፍጠር፣
- መልዕክትን መደጋገም

## 5.3 የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚዩኒኬሽንና የግንዛቤ ማስጨበጫ አፈፃፀም ስልቶች

የምዕተ ዓመቱን የትምህርት ዘርፍ የልማት ግቦች ለማሳካት ለሁሉም ህፃናት / አካል ጉዳተኞችና የትምህርት እድል ያላገኙ ህፃናትን ጨምሮ/ ጥራት ያለው ትምህርት በፍትሃዊነት ማዳረስ ያስፈልጋል። ይህንን እውን ለማድረግ የባለድርሻ አካላት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ ኖሯቸው፤ የትምህርት ፖሊሲውንና የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስትራቴጂን በቁርጠኝነትና በባለቤትነት መንፈስ እንዲመሩትና እንዲተገብሩት ማስቻል ያስፈልጋል። የነዚህን አካላት ግንዛቤ አድማስ ለማስፋት የተለያዩ የኮሚኒዩኬሽን አቀራረቦችንና ሥልቶችን መጠቀም ይገባል። ቀጥለው የቀረቡት ከዓለም ባንክ የኮሚዩኒኬሽን ሰነድ /2008 እኤአ/ የተወሰዱና ለዚህ ሥራ ምቹ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡ አቀራረቦች ናቸው።

**ማህበራዊ ግብይት** / Social marketing / የግብይት መሠረታዊ መርሆችን ለማህበራዊ ጉዳይ በመጠቀም ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የአቀራረብ ዘዴ እንደ የምልክት ቋንቋ መፃህፍት ፣ ስሌትና ስታይለስ ሥርጭት፣ በመሳሰሉ የትምህርት ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች ጉዳዮች ዙሪያ በሥፋት ሥራ ላይ የሚውል ነው።

Advocacy /**አድቮኬሲ**/: ሀገራዊ በሆኑ የተለያዩ ጉዳዮችና አጀንዳዎች ላይ ያተኩራል። ይህም ማለት የፖሊሲ አውጪዎችን በቀጥታ በማነጋገር / በማወያየት ወይንም የህዝቡን ድጋፍ በማሰባሰብ በፖሊሲዎች ላይ ማሻሻያዎችንና ለውጦችን በማምጣት ላይ ያተኩራል።

**የመረጃ ሥርጭት ዘመቻ** /Information dissemination and campaigns /: የተለያዩ የዕውቀት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችሉ መረጃዎችን በማሰራጨት ላይ ያተኩራል። ይህ አቀራረብ የአንድ አቅጣጫ የተግባቦት ሞዴልን /monologic model / በመጠቀም በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በአንድ ጊዜ ለብዙ ታዳሚዎች መልዕክት በማስተላለፍ ላይ ያተኩራል፣

**ትምህርትና ሥልጠና** /Education and training/: በሁለትዮሽ ተግባቦት ላይ የተመሠረተ ነው። ትምህርታዊ አቀራረብ ዕውቀትን በመጨመርና ግንዛቤ በማዳበር ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ የሥልጠና አቀራረቡ ደግሞ በጥቅሉ ሙያዊ ክህሎት በማሻሻል ላይ ያተኩራል።

**ተቋምን ማጠናከር** /Institutional strengthening/: በሥልጠና አማካይነት የተቋምን ውስጣዊ ብቃት ማጠናከርና ደረጃ በደረጃ በውጫዊ ታዳሚዎች ዘንድ የተቋሙን ገጽታ ማሳደግና ማሻሻል ላይ ያተኩራል፣

**የማህበረሰብ ንቅናቄ** /community mobilization/: ህብረተሰቡ በራሱ ወይም በተወካዮች አማካይነት ለኑሮው አስፈላጊ በሆኑና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በሚሰጡ ወሳኔዎች በንቃትና በባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፍ፣ እንዲወስንና የውሳኔዎቹን አፈፃፀም እንዲከታተል ለማስቻል የሚደረግ ሥልታዊ ጥረት ነው ።

**ትዕዛዛዊ ያልሆነ አሳታፊ ተግባቦት** /non-directive participatory communication /: ይህ ዓይነቱ አቀራረብ በሁለትዮሽ ተግባቦት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ በጋራ ክፍተቶችን መለየት፣ ዕቅዶችን ማዘጋጀት፣ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂ መቅረጽ፣ መተግበርና አፈፃፀሙን መከታተልን ያካትታል።

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ሠንጠረዥ የትኞቹን የኮሚኒዩኬሽን አቀራረብ መንገዶችና የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች በየትኞቹ የመልዕክት ዓይነቶችና ለየትኞቹ ታዳሚዎች መጠቀም እንደሚገባ የሚያሳይ ነው።

| **ታዳሚ** /Audiunce/ | **የችግሩ /የመልዕክቱ/ ዓይነት** (Problem situation) | **አቀራረብ** /Approach/ | **የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች** /Techniques recommended/ |
|---|---|---|---|
| ህብረተሰብና ተማሪዎች | አመለካከትና ግንዛቤ | **ማህበራዊ ግብይት** /Social marketing/ | ¬ ፖስተሮች፣<br>¬ ሚኒሚዲያ፣<br>¬ መሪ ቃሎች /banners/፣<br>¬ ብሮሸሮች፣<br>¬ የፓናል ውይይቶች፣<br>¬ አጫጭር የሬድዮና የቴሌቪዥን መልዕክቶች፣<br>¬ የጥያቄና መልስ ውድድር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ፕሮግራሞች<br>¬ ማህበራዊሚዲያ/facebook,የተንቀሳቃሽ ስልክ መልዕክቶች/<br>¬ ግጥም፣<br>¬ ድራማ፣<br>¬ ዶክዩመንተሪ ፊልም<br>¬ የገጽ ለገጽ ውይይት |
| ፖሊሲ አውጪዎችና ማህበረሰብ | የፖሊሲና የአመለካከት ክፍተት | Advocacy | ¬ የማህበረሰብ ውይይትና ስምፖዚየም<br>¬ የፓናል ውይይቶች<br>¬ ፖስተሮች,<br>¬ መሪ ቃሎች<br>¬ ብሮሸሮች,<br>¬ አጫጭር የሬድዮና ቴሌቪዥን መልዕክቶች<br>¬ የተንቀሳቀሽ ስልክ መልዕክቶች |
| ህብረተሰብ፣ አመራር፣ መምህራን፣ መያዶች፣ ተማሪዎች | አመለካከትና ግንዛቤ | የመረጃ ሥርጭት ዘመቻ /Information dissemination and campaigns / | ¬ የሬዲዮና ቴሌቪዥን መግለጫዎች፣<br>¬ ማህበረሰባዊ ውይይቶች<br>¬ የፓናል ውይይቶች<br>¬ መሪ ቃሎች /banners/፣<br>¬ ፖስተሮች፣<br>¬ ድረ ገፃችን መጠቀም<br>¬ ጋዜጣዎች<br>¬ መጽሔቶች<br>¬ ግጥም፣<br>¬ ድራማ፣<br>¬ ዶክዩመንተሪ ፊልም<br>¬ ስቲከርስ/Stickers/<br>¬ በተሽከርካሪ ላይ ሆኖ መቀስቀስ<br>¬ አመታዊ ሪፖርቶችን ማሰራጨት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ¬ ሰላማዊ ሰልፍ |
| ለመምህራን፣ ለትምህርት አመራርና ባለሙያዎች | የዕውቀትና ክህሎት ክፍተት | ትምህርትና ሥልጠና | ¬ የስራ ላይ ልምምድ<br>¬ አውደ ጥናት<br>¬ ሴሚናርስ<br>¬ የትምህርት ጉባኤዎችና የዕቅድ ክንውን ግምገማ መድረኮች<br>¬ ምርጥ ተሞክሮዎች<br>¬ የቡድን ውይይቶች<br>¬ አዳዲስ አሰራሮችና መረጃዎች ማስተዋወቂያ መድረኮች<br>¬ የገጽ ለገጽ ገለፃ<br>¬ የአተገባበር መመሪያዎች<br>¬ የተቋማት ሥርዓተ ትምህርት |
| ማህበረሰብ ወይም የማህበረሰብ ተወካዮች /የሀይማኖት መሪዎች፣ ተሰሚነት ያላቸው ታዋቂ ግለሰቦች፣ ወዘተ/ መያዶች፣ | አመለካከትና ግንዛቤ | የህብረተሰብ ንቅናቄ /community mobilization / | ¬ የማህበረሰብ ውይይትና ስምፖዚየም<br>¬ ፖስተሮች,<br>¬ መሪ ቃሎች,<br>¬ ብሮሸሮች,<br>¬ ኮንፈረንሶች<br>¬ የፓናል ውይይቶች<br>¬ ቴሌቪዥን/ለከተማ/<br>¬ ሬዲዮ/ገጠሩን ለመርደስ/ |
| ባለድርሻ አካላት /ማህበረሰብ፣የአካባቢ አመራር፣ መያዶች፣ሲቪክ ማህበራት/ | አመለካከትና ግንዛቤ | ትዕዛዛዊ ያልሆነ አሳታፊ ተግባቦት /non-directive participatory communication/ | ¬ የማህበረሰብ ውይይትና ስምፖዚየም<br>¬ ፖስተሮች,<br>¬ መሪ ቃሎች,<br>¬ ብሮሸሮች,<br>¬ ኮንፈረንሶች<br>¬ ድረ ገፆች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ¬ ጋዜጣ |

## 6. በኮሚዩኒኬሽንና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 6.1 ትምህርት ሚኒስቴር

- ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሥራን መተግበር የሚያስችል አደረጃጀት እንዲኖር ያደርጋል፣
- የኮሚኒዩኬሽን ስትራቴጂና የአተገባበር መመሪያ ያዘጋጃል፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ ዙሪያ የሚከናወኑ የኮሚኒዩኬሽን ተግባራት በዕቅድ ተካተውና በበጀት ተደግፈው እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
- በክልል ደረጃ ያለው ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ ትግበራን በባለቤትነትና በቁርጠኝነት እንዲመራው ለማስቻል የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ወጥ የሆነ አመለካከትና የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፣
- በኮሚዩኒኬሽን መሠረታዊ መርሆዎች፣በአቀራረብ /Approaches/መንገዶችና የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣
- በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዙሪያ የኮሚኒዩኬሽን ሥራን ለመስራት በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ያመቻቻል፣
- በሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤዎች ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ጉዳይ እንደ አንድ የትኩረት አጀንዳ ተይዞ ውይይት እንዲደረግበትና የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝበት ያደርል፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሥልጠና በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጥ ከተቋማቱ ጋር በመመካከር ሥልቶችን ይቀይሳል፣
- በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራር አካላትንና መምህራንን አመለካከትና ግንዛቤ የሚያዳብሩ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ላይ የሚያጠነጥኑ አዳዲስ ሀሳቦች፣ አሰራሮችና መልካም ተሞክሮዎችን በቀመር ያስተዋውቃል፣ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው እንደተገበሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- አዲስ የሚገነቡ ዩኒቨርሲቲዎች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
- በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ላይ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፣
- ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ተጨማሪ ሀብት ያፈላልጋል፣
- የኮሚዩኒኬሽን ሥራን በተመለከተ በታቀዱ ተግባራት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣

### 6.2 ክልል ት/ቢሮዎች

- ትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሠረት ከክልል ት/ቢሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሥራን መተግበር የሚያስችል አደረጃጀት እንዲኖር ያደርጋል፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ ዙሪያ የሚከናወኑ የኮሚኒዩኬሽን ተግባራት በዕቅድ ተካተውና በበጀት ተደግፈው እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
- በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የኮሚኒዩኬሽን ስትራቴጂና የአተገባበር መመሪያ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ይተገብራል፣
- በዞንና በወረዳ ደረጃ ያለው የበላይ አመራር የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ፕሮግራም ስትራቴጂ ትግበራን በባለቤትነትና በቁርጠኝነት እንዲመራው ለማስቻል የጋራ መድረኮችን በማዘጋጀት ወጥ የሆነ አመለካከትና የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋል፣
- በኮሚዩኒኬሽን መሠረታዊ መርሆዎች፣ በአቀራረብ / Approaches/ መንገዶችና በመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎች በፌዴራል ደረጃ በሰለጠኑ አሰልጣኞች አማካይነት ለዞንና ለወረዳ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ሥልጠና ይሰጣል፣
- በክልል ደረጃ በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዙሪያ የኮሚኒዩኬሽን ሥራን ለመስራት በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ያመቻቻል፣
- የትምህርት ጉባኤዎች ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ጉዳይ እንደ አንድ የትኩረት አጀንዳ ተይዞ ውይይት እንዲደረግበትና የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝበት ያደርጋል፣
- በመምህራን ትምህርት ተቋማት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ሥልጠና በተጠናከረ መልኩ እንዲሰጥ ከተቋማቱ ጋር በመመካከር ሥልቶችን ይቀይሳል፣
- በትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ የተቀመሩ አዳዲስ ሀሳቦች፣ አሰራሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ለዞንና ወረዳዎች ያስተዋውቃል፣ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥመውና በዕቅድ ተካተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ የክልሉን መልካም ተሞክሮዎችንም በመለየትና በቀመር በዞንና በወረዳዎች ያስፋፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፣
- አዲስ የሚገነቡ ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣
- ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ማስፈፀሚያ ተጨማሪ ሀብት ያፈላልጋል፣
- የኮሚኒዩኬሽን ሥራን በተመለከተ በታቀዱ ተግባራት አፈፃፀም ላይ ለዞኖችና ወረዳዎች ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- ከወረዳዎች በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ለትምህርት ሚኒስቴር ያስተላልፋል

### 6.3 ወረዳ ት/ጽ/ቤቶች

- በትምህርት ሚኒስቴር ስታንዳርድ መሠረት በየትምህርት ቤቶቹ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት መምህራንን ይመድባል፣
- በወረዳው ውስጥ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ስትራቴጂ ትግበራ ዙሪያ የሚከናወኑ የኮሚዩኒኬሽን ተግባራት በዕቅድ ተካተውና በበጀት ተደግፈው እንዲከናወኑ ያደርጋል፣
- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን አተገባበር መመሪያን ይተገብራል፣ በየትምህርት ቤቱ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣
- በክልል ደረጃ በሰለጠኑ አሰልጣኞች አማካይነት ለወረዳና ለቀበሌ የትምህርትና ሥልጠና ቦርድ አባላት፣ ለወረዳ የትምህርት አመራርና ባለሙያዎች፣ ለት/ቤት አመራሮች፣ ለመምህራን፣ ለወላጆች፣ ለታዋቂ ግለሰቦችና ለሀይማኖት መሪዎች የአመለካከትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤት አመራርና መምህራን የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ስትራቴጂን በባለቤትነትና በቁርጠኝነት እንዲመሩትና እንዲተገብሩት ለማስቻል የአመለካከትና የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፣
- በወረዳ ደረጃ በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዙሪያ የኮሚኒዩኬሽን ሥራን ለመስራት በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ያመቻቻል፣
- በወረዳ የትምህርት ጉባኤዎች ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ጉዳይ እንደ አንድ የትኩረት አጀንዳ ተይዞ ውይይት እንዲደረግበትና የጋራ ግንዛቤ እንዲያዝበት ያደርጋል፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ በሀገርና በክልል ደረጃ የተቀመሩ አዳዲስ ሀሳቦች፣ አሰራሮችና መልካም ተሞክሮዎችን በዕቅድ አካቶ ይተገብራል፣ የወረዳውን መልካም ተሞክሮዎችንም በመለየትና በመቀመር በት/ቤቶች ያስፋፋል፣ ተግባራዊነታቸውን ያረጋግጣል፣
- ለልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ማስፈፀሚያ ተጨማሪ ሀብት ያፈላልጋል፣
- የኮሚዩኒኬሽን ሥራን በተመለከተ በታቀዱ ተግባራት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- የትምህርት ቤቱ ማህብረተሰብ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ አዎንታዊ አመለካከትና ግንዛቤ የሚያስጭብጡና ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ድጋፍ የሚያደርጉ ሁለት የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን በየትምህርት ቤቱ ይመድባል፣
- ከየትምህርት ቤቶች በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ላይ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር ለክልል ት/ ቢሮዎች ያስተላልፋል፣
- አዳዲስ የሚገነቡ ት/ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ነባር ት/ቤቶችም ምቹ እንዲሆኑ አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል፣ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣

## 6.4 ትምህርት ቤቶች

- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን አተገባበር መመሪያን ይተገብራል፣
- በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዙሪያ የኮሚኒዩኬሽን ሥራን ለመስራት በትምህርት ቤትና በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር ያመቻቻል፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ በሀገር፣ በክልሉና በወረዳ ደረጃ የተቀመሩ አዳዲስ ሀሳቦች፣ አሰራሮችና መልካም ተሞክሮዎችን በዕቅድ ውስጥ አካቶ ይተገብራል፣
- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎችን አቅዶ ይተገብራል፣
- የተለያዩ መድረኮችን /ለአብነት ኮንፈረንሶች፣ የትምህርት ቀን፣ ፓናል ውይይቶች /፣ የትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያን፣ ፖስተሮችን፣ መሪ ቃሎችን፣ ዶክዩመንተሪ ፊልም፣ ወዘተ በመጠቀም በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብና ወላጆች አመለካከትና ግንዛቤ ያሰፋል፣
- የአካል ጉዳት ክበባት ማቋቋምና የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን በማዘጋጀት /ግጥም፣ ድራማ፣ ፣ዘፈን፣ ወዘተ/ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማጎልበት፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ህጻናት ወደ ትምህርት ቤት ያስገቡ እና አስተምረው ለሥራ ያበቁ ወላጆች በትምህርት ቤት ደረጃ በሚዘጋጁ የተለያዩ መድረኮች ተገኝተው ልምዳቸውን ለህብረተሰቡ እንዲያካፍሉ ያደርጋል፣የማበረታቻ ሽልማትና እውቅና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- ወላጆች፣ የአካባቢ ህብረተሰብና ሌሎች ባለድርሻዎችን በማስተባበር የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢን ይፈጥራል፣
- ት/ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት መረጃዎችን አጠናቅሮ ይይዛል፣
- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት መረጃዎችንንና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶችን ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ያስተላልፋል፣

## 6.5 መደበኛና የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህራን

- ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት በፍላጎታቸው ዓይነት መለየትና መረጃ መያዝ
- የትምህርት ችግሮችን መንስኤዎች መለየትና መፍትሂዎችን መተለም፣
- ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎች ወላጆችን ለህፃናቱ በሚደረገው ድጋፍ ዙሪያ ማወያየት፣
- ከትምህርት ቤቱ አመራር ጋር በመሆን ትምህርት ቤቱ ለህፃናቱ ምቹ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- የአካል ጉዳት ክበብን ማስተባበር፤

- ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት በመምህራንና በሌሎች የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ሊደረግላቸው የሚገቡ ድጋፎችን መለየት፤
- በልዩ ፍላጎት/ አካቶ ትምህርት ዙሪያ በትምህርት ቤትና በባለድርሻ አካላት መካከል የተጠናከረ ቅንጅትና ትብብር እንዲፈጠር ከት/ቤቱ አመራር ጋር በመሆን መስራት፤
- በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሊከናወኑ የሚገባቸው የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ፣ ድርሻቸውን ወስደው ይተገብራሉ፣
- የትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያን፣ ፖስተሮችን፣ መሪ ቃሎችን፣ ወዘተ በመጠቀም በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ ከት/ቤቱ አመራር ጋር በመሆን የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብና ወላጆች አመለካከትና ግንዛቤ ያሰፋሉ፣
- በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ዙሪያ በሀገር ዐቀፍ፣ በክልሉና በወረዳ ደረጃ ተቀምረው የወረዱ አዳዲስ ሀሳቦች፣ አሰራሮችና መልካም ተሞክሮዎችን ይተገብራሉ፣
- የትምህርት ይዘቱ፣ አቀራረቡና ምዘና ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ ይሆን ዘንድ የበኩላቸውን ይወጣሉ፣

## 6.6 ወላጆች

- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የአመለካከትና የግንዛቤ ማዳበሪያ ሥራዎች አስመልክቶ ት/ቤቱ በሚጠራው ስብሰባዎችና የውይይት መድረኮች ላይ ይሳታፋሉ፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸውንና የትምህርት እድል ያላገኙ ህፃናትን ት/ ቤት አስመዝግበው ያስተምራሉ፣ ሌሎቹም ወላጆች እንዲያስመዘግቡ ያበረታታሉ፣
- ከትምህርት ቤት ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር የልጆቹን የትምህርት ሁኔታ ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፣
- ስለ ልጆቻቸው ባሕሪ ለትምህርት ቤቱና ለመምህራኑ መረጃ ይሰጣሉ፣
- ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን አስመልክቶ በትምህርት ቤት በተለይም በመምህራን የሚሰጡአቸውን ምክሮች ተግባራዊ ያደርጋሉ፣
- ከትምህርት ቤት ጋር ያቅዳሉ፣ በአተገባበሩም ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆቻቸውን አስተምረው ለቁም ነገር ያበቁ ወላጆች ልምዳቸውን ለህብረተሰቡ ያካፍላሉ፣
- የአካል ገዳት ያለባቸው ህፃናት ወላጆች ማህበር ያቋቁማሉ፣

## 6.7 የአካል ጉዳተኞች ማህበራት

- የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎችን ዕቅድ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይተቻሉ፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፣ ክፍተቶችን በመለየት ግብረመልስ ይሰጣሉ፣
- ሀገሪቱ በፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና አዋጆች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሰራሉ፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላሉ፣
- ተገቢ የሆኑ የኮሚኒዩኬሽን አቀራረቦችና ዘዴዎችን በመጠቀም በአካል ጉዳተኝነት ላይ የህብረተሰብ ግንዛቤ ያጎለብታሉ፣
- የፖሊሲ ማሻሻያ ሀሳቦችን ያመነጫሉ፣
- የውሳኔ ሰጪ አካላትን ያግባባሉ፣
- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናትና ወጣቶች የትምህርት፣ የሥልጠናና የሥራ ሥምሪት ሁኔታ ይሟገታል፣

## 6.8 ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

- በየደረጃው ለሚሰሩ የአመለካከትና የግንዛቤ ማጎልበቻ ሥራዎች የፋይናንስ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋሉ፣
- በኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች አተገባበር ዙሪያ በየደረጃው ካሉ የትምህርት ዘርፍ አካላት /ትምህርት ሚኒስቴር፣ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤትና ትምህርት ቤት ጋር በመተባበር ሥልጠናዎችን ያስተባብራሉ፣ ይሰጣሉ፣

# 7.ክትትልና ግምገማ

### *7.1 የክትትልና ግምገማ መሣሪያዎች:*

*የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አተገባበርን ለመከታተልና ለመገምገም በተለያዩ ደረጃዎች የተለያዩ የክትትልና ግምገማ መሣሪያዎችን መጠቀም ይቻላል። ሱፐርቪዥን፣ የክትትል ሪፖርቶች፣ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የግምገማ መድረኮች፣ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ፣ ዐመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሄት ዋና ዋናዎቹ ናቸው*

### *7.2 የክትትልና ግምገማ አተገባበር*

የኮሚዩኒኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አተገባበር ውጤታማነትን ለማረጋገጥ በየደረጃው ባሉ የትምህርት መዋቅራት፣ እንዲሁም በትምህርት መዋቅርና በሌሎች ባለድርሻዎች መካከል የተጠናከረና ቀጣይነት ያለው የግንኙነት ሥርዓት መኖር አለበት። ይህም ማለት እያንዳንዱ ባለድርሻ ግዴታውንና ኃላፊነቱን ለይቶና ተረድቶ መወጣት ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ባለድርሻዎች የኮሚዩኒኬሽን የሥራዎች የክትትልና ግምገማ ሥራ በሚከተለው መልክ ያከናውናሉ።

**በት/ሚኒስቴር ደረጃ**

- ወጥነት ያለው የክትትል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች/check lists/ ያዘጋጃል፣ ያስተዋውቃል፣ ክልሎች እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፣
- የሪፖርት ማቅረቢያ ፎርማቶችን አዘጋጅቶ ክልሎች እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፣
- በየወቅቱ ከክልሎች የሚደርሱትን ሪፖርቶች ይገመግማል፣ ወቅታዊ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ የክልል ትምህርት አመራርና ባለሙያዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማህበራት፣ መያዶችና የት/ሚኒስቴር አመራርና ባለሙያ የሚሳተፉበት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት ኮሚኒዩኬሽን ዕቅዶች አፈፃፀም ሂደት የሚገመገምበት መድረክ በማዕከል ያዘጋጃል፣ ግብረመልስ ለባለድርሻዎች ይሰጣል፣
- በየክልሉ በዓመት አንድ ጊዜ በመገኘት ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን (Supportive Supervision) ያደርጋል፣
- በሀገር አቀፍ የትምህርት ጉባኤ ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች አፈፃፀም እንዲገመገም ያደርጋል፣ በጉባኤው በተደረሰባቸው ስምምነቶችና በተያዙ አቅጣጫዎች መሠረት ዕቅዶች ተከልሰው ወደ ሥራ የሚተረጎሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የትምህርት ስታቲስቲክስ መጽሔት በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ላይ ተገቢ መረጃዎችን አካቶ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለባለ ድርሻ አካላትም ያሰራጫል፣

**በክልል ት/ቢሮ ደረጃ**

- ትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅቶ በሚልከው የክትትል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች/check lists/ ተጠቅሞ መረጃዎችን ያሰበስባል፣ ያስተላልፋል፣
- ትምህርት ሚኒስቴር በአዘጋጀው የሪፖርት ፎርም በመጠቀም በየሩብ ዓመቱ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ለትምህርት ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፣
- በየወቅቱ ከወረዳዎች የሚደርሱት ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ ወቅታዊ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ የወረዳ ትምህርት አመራርና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም በክልሉ የሚገኙ መያዶች የሚሳተፉበት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሂደት መገምገሚያ መድረክ በክልል ደረጃ ያዘጋጃል፣ ግብረመልስ ለባለድርሻዎች ይሰጣል፣

- በዓመት ሁለት ጊዜ ትምህርት ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ዕቅዶች አፈፃፀም ሂደት መገምገሚያ መድረክ ላይ ይሳተፋል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፣
- በየወረዳ በዓመት ሁለት ጊዜ በመገኘት ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን (Supportive Supervision) ያደርጋል፣
- በክልል ደረጃ በሚዘጋጁ የትምህርት ጉባኤዎች ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች አፈፃፀም እንዲገመገም ያደርጋል፣ በጉባኤው በተደረሰባቸው ስምምነቶችና በተያዙ አቅጣጫዎች መሠረት ዕቅዶች ተከልሰው ወደ ሥራ የሚተረጎሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- የክልሉ ዓመታዊ የትምህርት ስታቲስቲክስ መጽሔት በልዩ ፍላጎት /አካቶ ትምህርት ላይ ተገቢ መረጃዎችን አካቶ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ለባለ ድርሻ አካላትም ያሰራጫል፣

**በወረዳ ት/ጽ/ቤት ደረጃ**

- ትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅቶ በሚልከው በክልሉ ት/ቢሮ ተረጋግጦ በሚተላለፍለት የክትትል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች/check lists/ ተጠቅሞ መረጃዎችን የሰበስባል፣ ያስተላልፋል፣
- ትምህርት ሚኒስቴር በአዘጋጀውና በክልሉ ት/ቢሮ ተረጋግጦ በሚተላለፍለት የሪፖርት ፎርም በመጠቀም በየሩብ ዓመቱ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ለት/ቢሮ ሪፖርት ያቀርባል፣
- በየወቅቱ ከት/ቤቶች የሚደርሱትን ሪፖርቶች ይገመግማል፣ ወቅታዊ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ የትምህርት ቤት አመራርና የልዩ ፍላጎት መምህራን፣ እንዲሁም በወረዳ የሚገኙ መያዶችና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ባለድርሻዎች የሚሳተፉበት የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሂደት መገምገሚያ መድረክ በወረዳ ደረጃ ያዘጋጃል፣ ግብረመልስ ለባለድርሻዎች ይሰጣል፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ የክልሉ ት/ቢሮ በሚያዘጋጀው የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ዕቅዶች አፈፃፀም ሂደት መገምገሚያ መድረክ ላይ ይሳተፋል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፣
- በየትምህርት ቤቱ በዓመት አራት ጊዜ በመገኘት ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን (Supportive Supervision) ያደርጋል፣
- በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጁ የትምህርት ጉባኤዎች ላይ የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች አፈፃፀም እንዲገመገም ያደርጋል፣ በጉባኤው በተደረሰባቸው ስምምነቶችና በተያዙ አቅጣጫዎች መሠረት ዕቅዶች ተከልሰው ወደ ሥራ የሚተረጎሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

**በት/ቤት ደረጃ**

- በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በሚልከውና በወረዳ ት/ጽ/ቤት ተረጋግጦ በሚተላለፍለት የክትትል የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች/check lists/ ተጠቅሞ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ለወረዳው ት/ጽ/ቤት ያስተላልፋል፣
- ትምህርት ሚኒስቴር በአዘጋጀውና በወረዳ ት/ጽ/ቤት ተረጋግጦ በሚተላለፍለት የሪፖርት ፎርም በመጠቀም በየሩብ ዓመቱ በልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ለወረዳ ት/ጽ/ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣
- በዓመት ሁለት ጊዜ የወረዳው ት/ጽ/ቤት በሚያዘጋጀው የልዩ ፍላጎት / አካቶ ትምህርት የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሂደት መገምገሚያ መድረክ ላይ ይሳተፋል፣ የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፣
- በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጀው የትምህርት ጉባኤዎች በተደረሰባቸው ስምምነቶችና በተያዙ አቅጣጫዎች መሠረት የት/ቤቱን የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ በመከለስ ይተገብራል፣
- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ፣ በወላጆች፣ በአካባቢው ህብረተሰብና ሌሎች ጉዳዩ በሚለከታቸው ባለድርሻዎች በዓመት ሁለት ጊዜ የትምህርት ቤቱን የኮሚኒዩኬሽን ሥራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ያስገመግማል፣ ባጋጠሙ የአፈፃፀም ችግሮች ላይ የጋራ መፍትሄ ያፈላልጋል፣

## ማጣቀሻ

Elena Maria, etal (2002) Communication for Social Change:
An Integrated Model for Measuring the Process and Its Outcomes, the Rockefeller Foundation,420 Fifth Avenue,New York, New York 10018-2702

Ministry of Education.2012.Educatuion Statistics Annual abstract 2003EC

(2010/11)

Ministry of Education.2010.Education Sector Development Programme IV

Project Cycle Management Gudelines.2004.(http://europa.eu.int/comm/europeaid)

Special Needs Education Programme in Ethiopia (2008) Inception report የወቅታዊ ሁኔታ ትንተና

The Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia .1995. Federal Democratic Republic Government of Ethiopia

World Bank.2008. Development Communication Suorce book: Broadening the Boundaries of Communication

World Health Organization.2011.World Report on Disability

UNESO.2005.Guidelines for Inclusion: Ensuring Access to Education for All

የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣1986፣ ትምህርት ሚኒስቴር

የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሃግብር ስትራቴጂ፣ 1998፣ትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርት አመራር አደረጃጀት፣ የህብረተሰቡ ተሳትፎና የፋይናንስ መመሪያ፣1994፣ትምህርት ሚኒስቴር